ሸይጧን በጀዚረተል ዐረብ (በባህር የተከበበው የዐረብ ምድር) ውስጥ ሰጋጆች ያመልኩኛል የሚለውን ተስፋ ቆርጧል። ነገር ግን በሰጋጆች መካከል ማጣላትን (ተስፋ አልቆረጠም)።

ከጃቢር (ረዺየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፦ "ሸይጧን በጀዚረተል ዐረብ (በባህር የተከበበው የዐረብ ምድር) ውስጥ ሰጋጆች ያመልኩኛል የሚለውን ተስፋ ቆርጧል። ነገር ግን በሰጋጆች መካከል ማጣላትን (ተስፋ አልቆረጠም)።"»
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በጀዚረተል ዐረብ ኢብሊስ ሰጋጅ አማኞች እርሱን ወደ ማምለክና ለጣዖት ወደ መስገድ ይመለሳሉ የሚለውን ተስፋ እንደቆረጠ፤ ነገር ግን በጭቅጭቅ፣ በፀብ፣ በጦርነት፣ በፈተናና በመሳሰሉት በመካከላቸው ለማጣላት ተስፋ ከማድረግ፣ ከመታገል፣ ከመልፋት፣ ከመስራትና ከመጣር አለተወገደም ብለው ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/8886